የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች(ኤሲፒኤስ) እና የጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ (GW) የህክምና እና የጤና ሣይንስ ት/ቤት (SMHS) ከፍተኛ ተፈላጊነት ባላቸው የጤና የሙያ መስኮች የስትራቴጂክ የህዝብ-የግል ትብብር የፈጠራ ትምህርት ለመስጠት አዲስ መሰረት እየጣሉ ነው ።

የአገረ ገዥው የጤና ባለሞያ አካዳሚ በቲ.ሲ ዊሊያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በጤና እንክብካቤ ሙያ በመሰልጠን እና በአካባቢውን የጤና ባለሞያ እጥረት ለመቅረፍ ለኮሌጅ ክሬዲት ነጥብ ማግኘት የሚያስችል የሙያ መስክ እንዲጀምሩ ያስችላል።

## ሰባት መንገዶች ከፍተኛ ተፈላጊነት ላላቸው ፤ የጤና ሙያ ስራዎች

**የአካዳሚ ተማሪዎች መከታተል ይችላሉ**

የአካዳሚ ተማሪዎች እስከ 18 የኮሌጅ ክሬዲት ከGW የህክምና እና የጤና ሣይንስ ት/ቤት(SMHS) ማግኘት ይችላሉ። ይህ መንገድ ከኮሌጅ ለመመረቅ የሚፈለገውን ጊዜ እና ገንዘብ በሚገባ ይቀንሳል። በተጨማሪም ለተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሲጨርሱ የተለያዩ ከፍተኛ ሙያ እና ከፍተኛ ተፈላጊ የሙያ ምርጫዎች በጤና ዘርፍ ይሰጣል ።

ተማሪዎች ከሰባት የሙያ መስኮች መካከል መምረጥ ይቻላሉ፤

- ባዮሜዲካል ኢንፎርማቲክስ
- የድንገተኛ ሕክምና አገልግሎቶች
- የህክምና ላቦራቶሪ ሣይንስ
- የነርስ ሙያ
- ፋርማሲ
- የስፖርት ህክምና
- የቀዶ ጥገና ቴክኒዎሎጂ

## የአገረ ግዢ እውቅና

በጁን 2018 አካዳሚው የአገረ ገዥው የጤና ባለሞያ አካዳሚ በሚል ስያሜ በቨርጅኒያ ኮመን ዌልዝ (በቨርጅኒያ የትምህርት ዲፓርትሜንት አማካኝነት ) ለሚከተሉት አላማዎች እውቅና ተሰጥቶል ፡

- ተማሪዎችን ለተመረጠ የሙያ ዘርፍ በማዘጋጀት እድሎችን ማስፈት
- የሙያ ዘርፍ ፍላጎት ማነቃቃት
- ብዙ ተማሪዎች ወደ ኮሌጅ ትምህርት እንዲሳቡ ማገዝ
- የሰው ሃይል ፍላጎት ማሟላት

## ለተማሪዎች አማራጮችን መሰጠት

**ከምረቃ በኋላ የሚኖሩ ምርጫዎች:**

- በጀማሪ ደረጃ በጤና ሙያ ዘርፍ ወዲያውኑ ስራ የማግኘት እድል ማስገኘት
- የዲፕሎማ ዲግሪ ለማግኘት ወደ ኮሚዩኑቲ ኮሌጅ እንዲገቡ ማስቻል
- ወደ GW የህክምና እና የጤና ሣይንስ ት/ቤት መዘዋወር ባለው የተረጋገጠ ተቀባይነት ስምምነት የኮሌጅ ክሬዲቲ እውቅና መሰረት የመጀመሪያ ዲግሪ ማግኘት ። ተማሪዎች የጤና ሣይንስ ሙያ ለመጨረስ የመረጡ ወይም በGW የህክምና እና የጤና ሣይንስ ት/ቤት የሙያ ፕሮግራም ለመመዝገብ የፈለጉ ለነፃ ትምህርት እድል ፣ ለበጋ ወራት ሥልጠና የኪስ ገንዘብ ክፍያ እና ለልዩ የአካዳሚ ማበልፀጊያ ፕሮግራሞች ብቁ ይሆናሉ።
- በGW እና በቨርጂኒያ እና በሜሪላንድ ከተመረጡ የኮሚዮኒቲ ኮሌጆች ጋር በትብብር የመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራም የማጠናቀቅ ፕሮግራም መግባት።

## የዩ.ኤስ. የጤና አገልግሎት እና የሃብት አስተዳደር ግራንት

አካዳሚው በሴፕቴምበር 2018 በዩ.ኤስ የጤና አገልግሎት እና የሃብት አስተዳደር ለጤና ሣይንስ ትምህርት ቤት የተሰጠ የ$3.2 ሚሊዮን ግራንት ሽልማት ዋና አካል ነው። የግራንቱ ገንዘብ የጤና ሙያ ዘርፍ እድል ፕሮግራም (HCOP) በGW የሚያመቻች ሲሆን ይህም የተዘጋጀው በዝቅተኛ የቤተሰብ ኑሮ ሁኔታ የመጡትን ግለሰቦች በትምህርት መስክ እንዲቀጥሉ እና የጤና ሙያ ዘርፍ እንዲገቡ ማገዝ። HCOP የሚያካትተው የገንዘብ ድጋፍ ፤ የኪስ ገንዘብ እና የነፃ ትምህርት ለHCOP አምባሳደር ተማሪዎች በተቀናጀ መልኩ በማበልፀጊያ ፕሮግራም ለሚሳተፉ ነው። የአምስት-ዓመት ፕሮግራም ተማሪዎች በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 11-12 ፤ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ሁለተኛ ዲግሪ እና ከወታደር - ጋር የተያያዘ ፕሮግራሞች ናቸው።

## ኤ ሲ ፒ ኤስ

የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች  ከ118 አገሮች የተውጣጡና 120 ቋንቋዎችን የሚናገሩ ከ15,000 በላይ ተማሪዎች አገልግሎት ይሰጣል። የትምህርት ቤት አስተዳደሩ 16 ትምህርት ቤቶች፤ 12 አንደኛ ደረጃ፣ ሁለት መካከለኛ ትምህርት ቤት፣ አንድ ቅድመ መዋእለ - 8ኛ ትምህርት ቤት እና የዓለም አቀፍ እውቅና ያለው ቲ.ሲ ዊሊያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አሉት። ከ4,000 በላይ ተማሪዎች በቲ.ሲ ዊሊያም የሚማሩ ሲሆን በቨርጂኒያ ካሉት ትላልቅ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል አንዱ ነው። ትምህርት ቤቱ የተውጣጣው በኢኮኖሚ፣ በትምህርት ፣ በዘር እና በጎሳ ከተለያየ ህዝብ ነው። የአገረ ገዢው አካዳሚ የመጀመሪያው ክፍል 100 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች
የቲ.ሲ ዊሊያም የተለያየ ህብረተሰብ ወኪሎች ናቸው።

ኤሲፒኤስ እያንዳንዱ ተማሪ ውጤታማ ይሁን የሚለውን ለማረጋገጥ ይህም በትምህርት አስተዳዳሩ የእይታ መግለጫ ላይ በአፅኖት ተገልፃል፤ "እያንዳንዱ ተማሪ ውጤታማ ይሁን፤ የእድሜ ልክ ተማሪዎችን እና የማህበረሰቡን ኋላፊነት ማበረታታት

## ጆርጅ ዋሽንግተን (GW) የህክምና እና ጤና ት/ቤት

በ1824 የተመሰረተው የGW የህክምና እና የጤና ሣይንስ ት/ቤት (SMHS) በዋሽንግተን ዲሲ የተከፈተ የመጀመሪያው የህክምና ት/ቤት ነው እና በአገሪቱ ደግሞ ደረጃ 11ኛ ነው።
በአገራችን ዋና ከተማ በሙሉ ልብና ቆራጥነት በመስራት የGW የህክምና እና የጤና ሣይንስ ት/ቤት ቁርጠኝነት አለው የአካባቢውን ፣ የብሄራዊውን የአለም አቀፍ ማህበረሰቡን የጤና እና ደህንነት ለማስጠበቅ ።

በህክምና እና የጤና ሣይንስ ት/ቤት ውስጥ የጤና ሣይንስ አዳዲስ ፈጠራና ተለዋዋጭ የትምህርት እና የምርምር ዲቪዝኖች አሉ። በዚህም የመጨው ትውልድ
መሪዎች በሰውነት ቴራፒ፣ በመልሶ ማቋቋም ሳይንስ ፣ በረዳት ሀኪም ትምህርት፣ በህክምና ላቦራቶሪ ሳይንስ፣ በጤና እንክብካቤ ሙያ ፣ በቁጥጥር ዘርፎች፣ የክሊኒክ እና የአደጋ መታደግ ስራዎች፣ የክሊኒክ አና ትራንስሌሽናል ምርምር እና በበርካታ ሌሎች ከጤና ጋር የተገናኘ ሙያዎች በመስልጠን ላይ ይገኛሉ። ከ45 በላይ ፕሮግራሞች እና የዲግሪ ዓይነቶች ከአሶሴት፣ ባችለር፣ ማስተርስ እና ዶክትሬት ደረጃ በጤና ሳይንስ ይሰጣሉ። የድህር ምረቃ ሰርትፍኬት ፣ ድርብ ዲግሪ፣ ጥንድ እና ወታደራዊ ግንኙነት ያላቸው ፕሮግራሞች እንዲሁም ፌሎሽፕ፣ ሪዚደንስ እና ከባካሎሬት በኋላ ሰርትፍኬት ይሰጣሉ።

---

*የጤና እንክብካቤ ስራዎች እስከ 2026 ድረስ በ18 በመቶ እድገት እንደሚያሳይ እና 2.3 ሚሊዮን አዳዲስ ስራውችን በአገር ደረጃ እንደሚጨመር ተገምቶል ። - ከማንኛውም የሙያ ዘርፍ በበለጠ*

የስራ ስታትስቲክስ ቢሮ

" የእኔ አያት የሳንባ ካንሰር ተይዞል ስለሆነም እኔ ከዚያ ጋር የተገናኘ አንድ ነገር ለማድረግ እያሰብኩ ነው ።" *የዚህ ዓይነት ፕሮግራም በመውሰድ እኔ የማስበው እኔ ሰዎችን መርዳት እችላለሁ በረዝም ጊዜ....እኔ የምፈልገው ፐልማኖሎጂስት መሆን ነው ምክንያቱም እኔ አይቻለሁ ይህ ስራ እንዴት የሰውን ህይወት እንዴት በአፋጣኝ እንደሚቀየር አይቻለሁ"*

የአካዳሚ ተማሪ ማያ ሎፔዝ

" እኔ ይህን ፕሮግራም እወደዋለሁ ምክንያቱም የወደፊቱን የሙያ ዘርፍ ምርጫ ያመለክታል። *የእኔ እህት እድሜዋ 21 ነው እንደእኔ ተመሳሳይ ዓይነት ቦታ ናት እኔ ወደ ዘጠነኛ ክፍል ስሄድ ። ይህ ፕሮግራም በጠም ቆንጆ ነው ምክንያቱም እንተ ቀደምህ ሂደሃል ።"*

የአካዳሚ ተማሪ ኤሪን ሐዋርድ

---

School of Medicine & Health Sciences
THE GEORGE WASHINGTON UNIVERSITY

ACPS Alexandria City Public Schools

ስለአካዳሚ ለተጨማሪ መረጃ ይህን ይጎብኙ፤
**smhs.gwu.edu/hssp**

**www.acps.k12.va.us/healthsciences**